# አዲስ ዘመን

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ሕዳሴ ይተጋል!

76ኛ ዓመትቁጥር 234 | ማክሰኞ ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም | ያንዱ ዋጋ 4 ብር




## ኢኮኖሚ

# ለመኖ ልማት የተገኘ ምቹ ሁኔታ

ዘላለም ግዛው

በእንስሳት ሀብቷ በዓለም ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትሰለፈው ኢትዮጵያ ዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (International Livestock Research Institute - ILRI) መቀመጫውን አዲስ አበባ ከተማ ለማድረጉም ምክንያቱ ይሄው እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ አገሪቱ በአፍሪካ በእንስሳት ሀብቷ ቀዳሚ ትሁን እንጂ ከዚህ ሀብት የምታገኘው ጥቅም በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የእንስሳት ሀብት ልማቱ ለአገሪቷ ኢኮኖሚ ዕድገት የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን በስፋት በማልማት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ሰፊ ሥራ መሠራት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ለዚህም የመኖና የውሃ ችግር መፈታት ይኖርበታል ፡፡ በተለይ የአገሪቱን የእንስሳት እርባታ በዝርያና በመኖ ለማሻሻል ትኩረት መደረግ አለበት፡፡ የተፈጥሮ ግጦሽና የመኖ ችግርን በመፍታት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውን ሲሆን፤ የብዝሃ ሕይወት ሀብትን ጠብቆ ለማቆየትም ፋይዳው የጎላ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

በሀገሪቱ የእንስሳት ሀብት ዘንድ ያለውን የመኖ ችግር እንደሚፈታ ትልቅ እምነት የተጣለበት እና ዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት በአዲስ አበባ ያስገነባው ዘመናዊ የዘረ መል ባንክና የባዮ ሳይንስ ማዕከል ሰሞኑን በይፋ ተመርቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ ማእከሉ አንድ ሺ ዓይነት የዕፅዋት ዝርያዎች ያሏቸውን 19ሺ ያህል ዘረ መሎችን ያሰባሰበና ለመላው ዓለም አገልግሎት የሚሰጥም ነው፡፡

የዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት ጅን ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጄን ሃንሰን እንደሚሉት፤ የእንስሳት መኖ በከተሞች መስፋፋት ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ ለመመናመን ከመጋለጡ በተጨማሪ በዓይነቱም እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የዘረመል ማዕከላት የእንስሳት መኖን በመንከባከብና በመጠበቅ ለቀጣይ ትውልድ ጠብቆ በማቆየት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ ባንኩ ለእንስሳት መኖ የሚያገለግሉ የተለያዩ የሳር ዝርያዎችንና ዕጽዋትን ይንከባከባል፡፡

ባለፉት ዓመታት 19 ሺ ለእንስሳት መኖ የሚውሉ አዝርዕት መለየታቸውን ጠቅሰው፣ ኢንስቲትዩቱ እነዚህን ለልማት ለማዋል እየሰራ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡ በየዓመቱ አንድ ሺ ያህል የእንስሳት መኖ ናሙናዎች ተለይተው ለምርምር እንደሚቀርቡም አመልክተው፣ በምርምሩም የኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ዋና ሥራ አስኪያጁ ይገልጻሉ፡፡

የኢንስቲትዩቱ የፕሮግራም ዳይሬክተር ክሪስ ጆንስ እንደሚናገሩት፤ ላለፉት 35 ዓመታት የተሰባሰቡትን የአዝርዕት ዝርያዎች ለማራባት አዳዲስ አሠራሮች



ፎቶ - በሃዱሽ አብርሃ

*የዘረመል ባንኩ አገር ውስጥ መቋቋሙ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩ ዕድል ይከፍትላቸዋል፤*

እየተተገበሩ ናቸው። አዝርዕቱ በማንኛውም ሁኔታ ሊበቅሉ የሚችሉ ለግብርናው ዘርፍ ዕድገት ጉልህ ሚና የሚጫወቱ፣ በምግብ ይዞታቸው ከፍተኛ ንጥረ ነገር ያላቸው፣ በሽታ መቋቋም የሚችሉና በዓይነትና በብዛት ከዚህ በፊት ከነበሩት ይልቃሉ፡፡ ዝርያዎችን በማዳቀል የተሻሻሉ የእንስሳት መኖዎችን ለማምረት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የእንስሳት ምርምር ዳይሬክተር ዶክተር ጌትነት አሰፋ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ይህ ዘመናዊ የመኖ ጂን ባንክ በአገሪቱም ሆነ በሌሎች አገሮች ያሉት የመኖ ዘሮች ተሰብስበው የተቀመጡበትን ለተጠቃሚዎችም የሚከፋፈሉበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት አዲስ የተከፈተውን ያህል ስብስብ እንደሌለውም አብራርተው፣ ኢንስቲትዩቱ በብዛት ያለው የምግብ ሰብል ዘሮች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

እንደ ዶክተር ጌትነት ገለጻ፤ ዘሮቹን ለምርምር የሚፈልጉ አገራት ሁሉ መውሰድ የሚችሉ ሲሆን፤ ባንኩ በአዲስ አበባ በመቋቋሙ ከቅርበት አኳያ ኢትዮጵያ በግንባር ቀደም ተጠቃሚ መሆን ትችላለች፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የክልልና የፌዴራል የምርምር ተቋማት እንዲሁም ሌሎች በመኖ ላይ ምርምር የሚሰሩ አካላት የመኖ ዘር በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ፡፡ በአንድ ጊዜ አንድ ሺ ዓይነት የዕፅዋት ዝርያዎች ወስዶ በየሥነ ምህዳሩ በመሞከር በምርታማነቱ፣ በጥራቱ፣ በተላማጅነቱ የሚፈለጉትን በመምረጥ አብዛኞቹ ለቀጣይ ሥራ የሚውሉበትን ዕድል ለመምረጥ ያስችላል፡፡

በረሃማነት እየተስፋፋ ነው፣ የመሬት መራቆት በስፋት ይስተዋላል፤ በጎርፍ እና በተመሳሳይ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ሳቢያ ለከብቶች መኖ የሚውል ግጦሽ እየጠፋ ነው፡፡ አሁን ያለው የሳር ዓይነት ከብቶች ብዙም ለመኖነት የማይመርጡትና የማይመገቡት ነው፡፡ በየአካባቢው ያለው የአየር ንብረት ተለያይነት አለው፡፡ በመሆኑም የመኖ ዝርያ ለመጥፋት ተጋልጧል፡፡

የመኖ ዝርያው በባንኩ ሲቀመጥ ሊጠፉ ይችላል የሚለው ስጋት ይወገዳል፡፡ በተለያዩ ቦታዎች የሚቀመጥ እንደመሆኑም፤ ለየአካባቢው ሥነ ምህዳር አማራጭ የሚሆን ዝርያ ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡

በጂን ባንክና የባዮ ሳይንስ ማዕከል የተቀመጠው ጠቅላላ ዝርያ በኮሎምቢያና ደቡብ አሜሪካ በሚገኘው የዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር የኢንስቲትዩት ማዕከልም የሚገኝ ሲሆን፣ ይህ ለዝርያዎቹ መጠበቅ የሚደረገው ጥንቃቄ ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሂደቱ መጪው ትውልድ እንዲጠቀምበት ያደርጋል፡፡ ዝርያው ከጠፋ በድጋሚ ማግኘት አይቻልም፡፡

በምድር ላይ ከነበሩ እንስሳት እጅግ ግዙፍ የተባለው የዳይኖሰር ዝርያ እንደነበረ ከመግለጽና በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች ቅሪተ አካሉ በተለያየ ጊዜ ከመገኘቱ ባለፈ ዝርያውን መተካት አልተቻለም፡፡ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ቢሆን ኖሮ ማቆየትም መመለስም ይቻል ነበር፡፡

እንደ ዶክተር ጌትነት ማብራሪያ፤ የግጦሽ መሬት እየጠፋ የሕዝብ ብዛትም እየጨመረ ነው፡፡ በግ እና ፍየል ሳይደመርበት የከብት ቁጥር ከ56 ሚሊዮን በልጧል፡፡ ይህ ሲሆን የመሬት መጠን ግን እንደ ቀድሞው ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ መሬቱን እያጠበቡት ይገኛሉ፡፡ የሰብል ተረፈ ምርት እንዲሁም የግጦሽ መሬት ውስን ናቸው፡፡ በመሆኑም ለወደፊት የእንስሳት ሀብት ልማቱ የመኖ ልማትን ከማካሄድ ውጪ ሌላ አማራጭ የለም፡፡ ለዚህም የጂን ባንክና የባዮ ሳይንስ ማዕከሉ እንደ አንድ አማራጭ ይወሰዳል፡፡

አርሶ አደሩ በቀዳሚነት ራሱን መመገብ ስላለበት ባለው መሬት ሰብል ያመርታል፡፡ የሰብል ምርቱ እየተሻሻለ ሲሄድ የወተትና የስጋ ፍላጎት ይመጣል፡፡ በቀጣይነት ሕዝቡም አገሪቱም ከእንስሳት ሀብት መጠቀም አለባቸው፡፡ በእንስሳት ሀብቱ ላይ በትኩረት ከተሰራ ከአገር ውስጥ ፍላጎት ተርፎ ለውጭ ገበያ የሚተርፍ ምርት ሊገኝ ይችላል፡፡

የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ገብረእግዚአብሔር ገብረዮሐንስ፤ አገሪቱ ባላት የተለያየ ስነ ምህዳር ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ የሳር ዝርያዎች እንደሚበቅሉም ይገልጻሉ፡፡ ባንኩ ዘረ መል የሚቀመጥበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ዘረ መል በጥንቃቄ ሲቀመጥ አሁን ላለውም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የሚተርፍ ይሆናል ይላሉ፡፡

እንደ ዶክተር ገብረእግዚአብሔር ማብራሪያ፤ አገሪቱ የእነዚህ የሳር ዘረ መል ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም፣ የግጦሽ መሬት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የአፈር መሸርሸርና ድርቅ እየተከሰተ ይገኛል፡፡ በዚህ ሳቢያም ይህን ሀብት እንድናጣ ያደርጋል፡፡ ይህን ለመከላከል ዘሩን በዘረ መል ባንክ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

አንድ ዘር በባንኩ እስከ 25 ዓመታት መቀመጥ ይችላል፡፡ በየጊዜው የመብቀል አቅሙ እየተረጋገጠ ከተወሰነ ዓመታት በኋላ በድጋሚ ተሰብስቦ እየተዘራ የሚገባበት ሥርዓት ይኖራል፡፡ ዘሩ ለቀጣይ የልማትና የምርምር ሥራም የዘር ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ባንኩ ቀደም ሲልም በተወሰነ አቅም አገር ውስጥ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፣ አሁን ዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት ባቋቋመው ደረጃ መከፈቱ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርም ይናገራሉ፡፡

ባንኩ ለኢትዮጵያ ብቻም ሳይሆን ለዓለም አገራት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የሚሰበሰበው ዘር የአገር ውስጥ ብቻ ሣይሆን የሌሎች አገሮችም ጭምር መሆኑን የሚናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአንድነት ተሰብስቦ መቀመጡ የሌሎች አገሮች ዘረ መልን በቅርበት አግኝተን ለመጠቀም ይረዳናል ይላሉ፡፡ «የራሳችንን ለማስቀመጥም የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ሲከሰት ዘሮች እንዳይጠፉ ያደርጋል፣ ለተለያዩ ሥነ ምህዳሮች የሚስማሙ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማካሄድም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል» በማለት ፋይዳውን ዶክተር ገብረ እግዚአብሔር ያብራራሉ፡፡

እንስሳት በተለምዶ የሚመገቡት የሰብል ተረፈ ምርቶችን ነው፡፡ ይህ ግን በቂ አይደለም፡፡ የእንስሳት ሀብቱና የዝርያቸው ዓይነት ጥሩ ቢሆንም፣ በመኖ እጥረት ምክንያት የሚጠበቀውን ያህል ተጠቃሚ መሆን አላስቻለም፡፡ የወተት ምርቱም ዝቅተኛ ነው፡፡

ይህን ለመቀየር መኖ ላይ ትልቅ ተግባር መከናወን አለበት ተብሎ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ መኖ ሲባል ልቅ ግጦሽ አይደለም፡፡ ዘመናዊ የሆነ የመኖ ልማት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የዘረ መል ባንኩ ትልቅ አቅም ይፈጥራል፡፡ በተለያየ ምክንያት ምርቱ የቀነሰ የግጦሽ መሬት መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ባንኩ በአደጉት አገራት የተለመዱ ዝርያዎችን በቅርበት በማግኘት በአገር ውስጥ ለማልማት ትልቅ ዕድል ይከፍታል፡፡

ዓለም አቀፉ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት ከእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴርና ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡ ላለፉት 40 ዓመታትም በጋራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በተቋሙ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችን ወደ አርሶ አደር በማድረስ በኩል እኛ የምንሰራቸው ሥራዎች አሉ፡፡ ወደፊትም በተመሳሳይ መልኩ የቅንጅት ሥራው ይቀጥላል፡፡ ተቋሙ ዓለም አቀፍ የምርምር ተቋም እንደመሆኑ ትልቅ አቅም አለው፡፡ የአገር ውስጥ አቅም በመገንባት፣ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች በኢንስቲትዩቱ የምርምር ሥራ እንዲሰሩ በማድረግ ትልቅ እገዛ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የሌሎች አገሮች ዘረ መልን በቅርበት አግኝቶ ለመጠቀምም ሆነ አገር ውስጥ ያሉትን ዕጽዋት ለረጅም ጊዜ ለማስቀመጥ የጎላ ፋይዳ እንደሚኖረው ተስፋ የተጣለበት ይህ ዘመናዊ የዘረ መል ባንክና የባዮ ሳይንስ ማዕከል፣ የአየር ንብረት ለውጥ ሲከሰት ዘሮች እንዳይጠፉ ለማስቀመጥ፡፡ ለተለያየ ሥነ ምህዳር የሚስማሙ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን ለመስራትም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ «በእጅ ያለ ወርቅ ነው» እንደሚባል በችልተኝነት በመዘናጋት ይህን ምቹ ሁኔታ በሚገባ ለመጠቀም የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ባለሙያዎች በትኩረት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡